# የቅማንት ጉዳይ ለኢሕአዴግ እንደ ዕንቁ ነው

ከ 1983 ዓ/ም አንስቶ ኢትዮጵያን እያዋከበና ሕዝቦችዋንም እርስ በ እርስ እያጨፋጨፈ ያለው የትግራይ አክራሪ ዘረኞች የፃፉት ማኒፌስቶን ተገኑ አድርጎ የተመሰረተው ኢሕአዴግ ዋና አላማው አገሪቱን መበጣጠስ ብቻ ነው። በዚህ ስራ ላይ ደግሞ ብትንትናቸው እንዲወጣ በውሳኔ የተፈረጁት የአማራው ጎንደር፤ ሸዋ፤ ወሎና ጎጃም ናቸው። አማራውን እየወገረና በልማት ወደ ሁዋላ ጎትቶ እርቃኑን የሚቀር የደሆች ደሀ ለማድረግና በኦሮሚያና በትግራይ ሌሎች ማህበረሰቦች መብቶች እንዳይኖራቸው በአማራው አገር የሚኖሩት እንደ ቅማንት ዓይነቶች ደግሞ ማንነታቸው ደምቆ የአማራውን አንጡራ መሬቶች ተቀራምተው ራሳቸውን ያስተዳድሩ በሚል ሽፋን ቂሎ ማሞ እያሉ የሚሳለቁበት አቃፊው አማራ ተገዝግዞ እንዲጠፋ እስከዛሬ በወያኔ ዙፋን ላይ ቂጥጥ የማለት እድል የተሰጣቸው ጠቅላይ ሚኒስትሮችና የብ አ ዴ ን አዴፓ የበሉበትን ወጪት ሰባሪ ባለስልጣኖች ሲጫወቱበትና ሲበጣጥሱት ኖረዋል አሁንም የለወጡት አሰራር ፈፅሞውን የለም። አሁን ማዕከላዊ የፖለቲካ ስልጣን ላይ የተቀመጠው ዶ/ር አህመድ ጥቅምት 29/2011 ጎንደር ላይ ሰዎችን ሰብስበው ነበር። ተሰብሳቢዎቹ ደግሞ የአገር ሽማግሌ ወዘተ. የሚባሉና የቅማንት ነፍስ በላ የወያኔ ተላላኪዎች ሲሆኑ የወልቃይት አማራ ማንነት ኮሚቴ አባላትም በተናጠል የውይይት ዕድል አግኝተው እንደነበር የዶ/ር አህመድ ፐሬስ ዋና ፀሐፊ ተናግረዋል። እስቲ ዶ/ር አብይ አህመድ ስለቅማንቶች ምን አሉ? ቅማንቶችስ የጠየቁት ምን ነበረ? በዚህ ሰላሙን በያቅጣጫው ላጣውና በኢትዮጵያ ተዋክቦ እንዲኖር አለያም ጭራሽ እንዲጠፋ ወያኔ ኢሕአዴግ ለፈረጀው አማራ የኢሳያስና አብይ የጎንደርና ባህርዳር ጉብኝት ፋይዳው ምን ይሆናል ትላላችሁ? ኢሳያስን ከነሸአብያ ጭምር አማራው ላይ ያላቸውን አቅም እናውቀዋለን። ከእንግዲህ ወዲህ አዲሱ የአማራ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ወሳኝ የሆነው ወጣት ትውልድ " ወልቃይት የኛ ነው!!! " እያለ ማንነቱን ለነአብይና ኢሳያስ በጎንደሩ አቀባበል ሳያወላውል ለዝውም ፒያሳ ላይ እንዲያውቁለት ማድረግ ችሎዋል። ሕዝቡ በነቂስ አደባባይ የወጣው በአማራው መሬት ላይ የሚደረገውን ዝርፊያ እንዲቆምና ግዜውም ሲደርስ ሳይወዱ በግድ እንደሚያስመልስ በርግጠኝነት እንዲያውቁት ያለውን መልዕክቱን ለማስተላለፍ ብቻ ስለነበር ለአማራ ትልቅ የሆነ ቀን ውሎለታል።

ከዕለታት አንድ ቀን ብአዴን አዴፓ ለአማራው የሚከተለውን ብያኔ አስተላልፌብሀለው የሚል መልዕክት እንዲህ ብሎ አደረሰው ". . . ቅማንት የራሱ ስነልቦናዊ አመለካከትና ባህል ያለው አማራ ያልሆነ በኩታ ገጠም የሚኖር ብሔረሰብ ነው። የፌዴሬሽን ም/ቤትም ይህን ቦታው ድረስ ሄዶ አረጋግጦ ወሳኔ አውጥቶበታል። በአማራ ም/ቤትም የሕዝብ ተወካዮች ራሱን እንዲያስተዳድር ከአርማጭሆና ከጭልጋ 42 ቀበሌዎችን ሰጥተነዋል። " ወይ ብ አ ዴ ን! ቅማንትና አማራን መለየት እንደማይቻል ልባችን ቢያውቀውም የአዴፓው ያለው አባተ በወያኔ ትዕዛዝ ቅማንት ራሱን የቻለ ማንነት ያለው ብሔረሰብ ነው እንዲባል አዲስ አበባ ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሆኖ አስወሰነላቸውና አምባሳደር ተብሎ ተሾመ። አንድ ሰሞን ደግሞ የሕዝበ ድምጽ በፌደራል ሀላፊነት ተካሄደ ተባለና አማራው በነቂስ ወጥቶ ያዋረዳቸውን ስናስብ ደግሞ መፅናናት እናገኛለን፡፡ እነርሱ ግን ይህንንም የራሳቸውን ድራማ ረስተውታል። ከዛም ቀጥሎ አዴፓ ኮሽታ ሳያሰማ በ 42 ቱ ላይ 17 ጨመረባቸውና የሚመሰረተው አስተዳደር 69 ቀበሌዎችን ያቀፈ ነው ብሎን ቁጭ አለ። አሀ!

ይሄም አለ ለካ አሉና እነቅማንቶች 3 ይጨመርልን ብለው አማራውን ወያኔ ባስታጠቃቸው ከባድ መሳሪያ ደሙን አፈሰሱት። ደርግ ሲወድቅ ከሱዳን የገቡት የወያኔ ወታደሮች በመተማና አርማጭሆ በብዛት በቅራም በመጠኑ አማራውን እያፈናቀሉ የሰሊጡን እርሻ ንግዱንም ሁሉ አንቀው በመያዝ እንጣጥ ያሉ ሀብታም ሆኑ። መሳሪያና የፖለቲካ ድጋፍ ከፌደራል መንግስትና ከወያኔ ስለሚሰጣቸው ማን ይቻላቸው። ጭራሽ ብድግ አሉና መተማ፤ አብርሀጅራና አብደራፊ የትግራይ ናቸው በሚል ባደባባይ የይገባኛል ጥያቄም እስከማቅረብ ደርሰው ነበር። ታዲያ ለወያኔ ማኒፌስቶ እውን መሆን ያገኙት ብልሀት ራሳቸውን ቅማንት ነን እያሉ ጎንደርን እስከ ትላንትናዋ ቀን ጥቅምት 29/2011 አማራውን ማስጨፍጨፍን ነበር። ለመሆኑ ቅማንቶች ትግሬዎችን ከወንድማቸው አማራ የመምረጥ አባዜ አዋጪ ነውን? የነገ ሰው ይበለንና ውሎ አድሮ የምናየው ይሆናል።

በዚህ ትርምስ ሕወሐት ታስረው የተፈቱና አሁን አመራር ላይ ያሉ የአማራ ክልል ሀላፊ የሆኑ በቅማንትና ትግሬዎች ላይ ማፈናቀል፤ የንብረት መውደምና ግድያ ስለፈጸሙ በሕግ ይጠየቁ ብሎ 'ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሀል' እንደሚባለው ሙሾውን አቀለጠው። እነ ገዱም ድብስብስ ያለ የተቃራኒ የሚመስል ወኔ ቢስ መግለጫ አወጡ ተባለ። አማራው አሁንም ይገፋል ነገር ግን ዝም ስለሚልና አጠፌታዊ ራስን የመከላከል እርምጃ ስለማይወስድ በሌሎች ቦታዎች የሚደርስበትን ጥፋት ለግዜው አናንሳውና በራሱ የጎንደር መሬት ላይ ትግሬዎችና ቅማንቶች ቅርምት ውስጥ ጭልጥ ብለው ገበተውበታል። እነ ደመቀንና ገዱን ባናነሳቸው ሳይሻል አይቀርም ምክንያቱም ሱሪያቸውን አውልቀው ቀሚስ ከለበሱ 27 ዓመቶች አስቆጥረዋልና። እጅጉን የሚደንቀው በኦሮሞያ ያሉ ዘዮች፤ ወርጂዎች፤ አርጎባዎች፤ ጉራጌዎችና አማራዎች ራስን የማስተዳደር መብት ያስነፈጉት ዶ/ር አህመድ ትላንትና በጎንደሩ ስብሰባ " የቅማንት ራስ አስተዳደር ቶሎ መመስረት ይኖርበታል። የቅማንቶች ኮሚቴ የጠየቃቸው ተጨማሪ 3 ቀበሌዎችም መሰጠት አለባቸው። " አሉና አዴፓ ከ 42 ወደ 69 ያሳደገውን እርሳቸውም ከማን አንሼ ብለው ወደ 72 ቀበሌዎች እሳደጉትና እርፍ አሉ። ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ስልጣን ላይ ለዘላለም የሚኖሩ ይመስላቸዋል? የሚሰሩትን ስናይ ' እኔ ከሞትኩ ሳር አይብቀል ' የሚል አቅም ያላቸው ፈላጭ ቆራጮች እንደሆኑ ምንም አያከራክረንም። ቅማንቶችስ ቢሆኑ ያቺ ወያኔ ከነልቅምቃሚው ሲወድቅ ምን ይውጠኛል ብለው አይስቡም እንዴ? አማራው እንደሆን በአዲሱ ትውልድ ትግል ግዜው ሲደርስ ታሪኩን እንደሚያድስ ጥርጥር ስለማይገባን ዛሬ የደነሱብንና ያዋረዱን ' አይነጋ መስሎዋት ቐት. . . ' የምትባለውን እጣ ፈንታ መቅመሳቸው ግን ምን ግዜም አይቀርላቸውም። በአማራው ጥፋት ላይ ሕወሐት ታላቐ ትግራይን፤ ለኦነግ ሸዋና ወሎ ተጠቃሎ ኦሮሚያን፤ ለሱዳንም ቐራንና መተማን ተቀራምቶ የመመስረት አላማ በወጣቱና አዲሱ የአማራ ትውልድ ተጋድሎ ሕልም ብቻ ሆኖ ይቀራል። የአማራ ጠላቶች" አላርፍ ያለች ጣት. . . " ከሚለው የአማራ ቅኔ ትምህርት የምትወስዱበት ወቅት ላይ ሳትወዱ በግድ ደርሳችሁዋል! "የባጡን አወርድ ብላ የብብትዋን ጣለች " እንዳይሆንባችሁ።
አብነት ሁነኛው ነኝ!